የአማራ ህዝብ የህልውና ስጋት አለበት ሲባል….

መብቱን በከፊልም ሆነ በሙሉ የተነጠቀ ህዝብ ፈጥኖም ሆነ ዘግይቶ ለትግል መነሳቱ የማይቀር ነው። የዙፋናቸውን አራት እግሮች በህዝብ መብት ላይ ጭነው የተደላደሉ ጨካኝ አምባገነኖች ደግሞ ይህን አይቀሬ የህዝብ ትግል ቢችሉ ለማስቀረት፣ ካልሆነ ለማዘግየት፣ ካልተቻለም የተጀመረ የህዝብ ትግልን አልከስክሶ ለማስቀረት ደመነፍሳቸው ያዘዛቸውን ሁሉ ያደርጋሉ። ከዚህ ደመነፍሳዊ አካሄድ አንዱ የህዝብን የሚታይ በደል ሽምጥጦ መካድ፣ አሳንሶ ማቅረብ ወይንም ከሆነው በተቃራኒው አድርጎ አጣሞ ማቅረብ ናቸው። እንዲህ በማድረግ ህዝቡ በየእለቱ እየኖረ ያለውን የመከራ ኑሮ፣ ሞት፣ ስደት እና መፈናቀል እውነትነት እንዲተራጠር፣ እንዲደናገር እና ለትግል መነሳቱ ራሱ ትክክለኛ እርምጃ መሆን አለመሆኑን የመጠየቅ ውዥንብር ውስጥ እንዲገባ ያደርጋሉ።

ለትግል የተንሳው ህዝብ ለትግል ያስነሳው በደል መነሻው ከየት እንደሆነ፣ ለደረሰበት በደል ተጠያቂው ማን እንደሆነ ለይቶ አውቆ መታገል የሚገባውን አካል በግላጭ እንዳይታገል ብዥታና ድንጋሬ ውስጥ መክተት የጨቋኝ ረጋጭ እና ጨካኝ መንግስታት ባህሪ ነው። በሀገራችን በህውሀት እና ኦህዴድ/ኦነግ ቅብብሎሽ ለሰላሳ ሶስት አመታት የዘለቀው አማራ-ጠል ጨቋኝ ዘረኛ ስርዓት በአማራ ህዝብ ላይ ያደረሰውንና እያደረሰ ያለውን ፈርጀ-ብዙ በደል ህዝቡ ተረድቶ ለትግል እንዳይነሳ ይህንኑ የተለመደ ዘይቤ ይጠቀማል። ይህን ዘይቤውን ገቢራዊ ለማድረግ የተለያዩ መንገዶችን እያፈራረቀ ስራ ላይ ያውላል። ራሱ በሚዘውራቸው ሚዲያዎች በአማራ ህዝብ ላይ የሚደርሰውን በደል መካድ፣ በተቃዋሚ ፓርቲ ማሊያ የጭካኔው አጋር ያደረጋቸውን የስልጣን ጥመኛ ሹማምንት ማናገር፣ ገለልተኛ ሲል የሰየማቸው ተቋማት የዘር ማጥፋት ወንጀሉን አይተው እንዳላዩ እንዲሆኑ ማድረግ፣ አማራ-ጠሉ ስርዓት ከሚጠቀምባቸው ዘዴዎቹ ዋንኞቹ ናቸው።

የአማራን ህዝብ ትግል ለማስቀረት፣ ለማዘግየት ወይም ለማልከስከስ አማራ-ጠሉ ስርዓት አስቀድሞ የሚያጠቃው የአማራ ህዝብን ትግል በማዕከላዊነት የሚያሰባስቡ አጀንዳዎችን ባዶ ጩሀት በማስመሰል ነው። ከእነዚህ አጀንዳዎች ዋነኛው በአማራ ህዝብ ላይ የተቃጣው የህልውና አደጋ ነው። ይህ አደጋ አማራ የተባለን ሁሉ የሚያሰጋ ግልጽ እና ነባራዊ ሀቅ ነው። ለሰላሳ ሶስት አመታት በርካታ አማሮች በዘውግ ማንነታቸው ብቻ በህይወት የመኖር መብታቸውን ተነፍገዋል። እነዚህ ወገኖቻችን በአማራ ህዝብ ላይ የተቃጣውን የህልውና አደጋ ህይወታቸውን በማጣት ተጎንጭተውታል። ከእነዚህ ወገን ያልሆነው ሰፊው የአማራ ህዝብም

ከዚህ ስጋት ነጻ አይደለም። ይህን ማንነት ተኮር የህልውና አደጋ ታግሎ መቀልበስ እስካልቻለ ድረስ ማንኛውም አማራ በማንኛውም ጊዜ ህልውናውን የማጣት አደጋ ጽዋን ሊጎነጭ ይችላል። ይህን ሀቅ ለመካድ፣ ለማጥፋፋት እና ለማምታት አማራ-ጠሉ ጎራ ሁሉ በከፍተኛ ትብብር ጠንክሮ ይሰራል።

አማራ-ጠሉ ጎራ የአማራ ህዝብ የተጋረጠበትን የህልውና አደጋ ትርጉም የለሽ ለማስደረግ ሲሰራ በተቃዋሚም ሆነ በገዥ ፓርቲ ስም ያሉ አጋሮቹን እና በሚዲያ እና በምሁርነት ስም የሚያጆቡትን አጃቢዎቹን ሁሉ ጥቅም ላይ ያውላል። እነዚህ የአማራ-ጠሉ ጎራ ስውርም ሆነ ግልጽ ሰልፈኞች አማራው የህልውና ስጋት የለበትም ሲሉ ለክርክራቸው ማጥበቂያ የሚሆኑ ፍርደ-ገምድል ክርክሮችን ያነሳሉ። በተለይ በምሁርነት ካባ ተሸሽገው የአማራ-ጠሉን መንግስታዊ የዘር ማጥፋት ወንጀል የሚደግፉ ወገኖች የሚያመጡት ክርክር ህዝብን የማደናገር አቅሙ ከፍ ያለ ነው። እነዚህ ምሁር ተብየወች አማራው የህልውና ስጋት እንደሌለው ሲያስረዱ የሚያመጡት የተለመደ ክርክር "አማራው ቁጥሩ ብዙ ስለሆነ የህልውና ስጋት አለብኝ ሊል አይችልም፤ ስለህልውና ስጋት ማንሳት ያለብት ቁጥሩ ትንሽ የሆነ ህዝብ ነው" የሚል ነው። የዚህን አባባል አይረቤነት እነዚህ ሰዎች ራሳቸው ባመጡት ክርክር ደረጃ ወርደን እናስረዳ ከተባለ እያሉ ያሉት "አንድ ቁመቱ ረዥም ሰው ቁመቱ መለሎ ስለሆነ ከወደ እግሩ የተወሰነ ሜትር ቢቆረጥለት የቁመተ--አጭሩን ሰው ያህል አይጎዳም እና የእግሩን መቆረጥ እንደ ችግር ማንሳት የለበትም እንደ ማለት ነው። በሌላ አነጋገር ቁመተ-አጭር እና ቁመተ-ረዥም ሰዎች ሁለቱም እግራቸው ቢቆረጥ ጉዳት ተብሎ መነገር ያለበት የቁመተ-አጭሩ ነው እንጅ ቁመተ-ረዥሙ ችግር ደረሰበት ማለት አይቻልም እንደማለት ነው። ይህ ምሁር ለተባለ ሰው ይጠፋዋል ማለት አይቻልም።

አይኑ በጥላቻ ላልታወረ ሁሉ የህልውና ስጋት መንስኤ የሆነው የዘር ማጥፋት ትርጉም በተባበሩት መንግስታት ፣ Genocide Watch እንዲሁም የተለያዩ ምሁራን በጻፏቸው መጸሀፍት ተቀምጧል። በእነዚህ ማጣቀሻዎች መሰረት ማንነትን መሰርት አድርጎ፣ ታስቦበት እና ተቀነባብሮ የሚደረግ ግድያ ሁሉ ቁጥሩ ትንሽም ሆነ ብዙ በሆነ ህዝብ ላይ ቢደረግ ዘር ማጥፋት የሚባል ትርጉም ይሰጠዋል። አንድ ህዝብ በማንነቱ ሳቢያ ተነጥሎ ዘር የማጥፋት ወንጀል ሰለባ ሆነ ማለት ደግሞ የህልውና ስጋት አለበት ማለት ነው። የህልውና ስጋት ማለት ህልው ሆኖ የመኖር መብት ጥያቄ ምልክት ውስጥ ገባ ማለት እንጂ ሌላ ነገር አይደለም። ህልው ሆኖ መኖር ማለት ደግሞ በህይወት የመኖር ጉዳይ ብቻ አይደለም።

የአማራ ህዝብ የህልውና ስጋት አለበት ማለት በሀገሩ ላይ በህይወት የመኖር መብቱን ጨምሮ በሀገሩ ላይ ህልው ሆኖ መታየት በሚገባው ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ፣ እና ባህላዊ መስኮች ላይ ሁሉ ህልውናው አደጋ ውስጥ ወድቋል ማለት ነው፡፡ የአማራ ህዝብ በህይወት የመኖር መብቱን ከመነጠቁ በተጨማሪ በሀገሩ ላይ በእነዚህ መስኮች ሁሉ ህልውናው ( existence) እንዳይኖረው ተደርጓል

አማራ-ጠሉ ስርዓት አማራው በሀገሩ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ እና ባህላዊ መስኮች ህልውና እንዳይኖረው ማድረጉን በኩራት የሚያወራው "ጀብዱ" ነው፡፡ የአማራ-ጠሉ ጎራ ፊት አውራሪዎች ህውሀት እና ኦህዴድ/ኦነግ አማራ ለሶስት ሽህ አመታት ወደ ስልጣን ዝር እንዳይል አድርገነዋል እያሉ በግልጽም በስውርም ሲያወሩ የአማራ ህዝብ በሀገሩ ላይ ሊኖረው የሚገባው ፖለቲካዊ ህልውና አደጋ ውስጥ ወድቋል ማለት ነው፡፡ በተመሳሳይ አማራ-ጠሉ ስርዓት የአማራ ጀግኖችን ሀውልት ሲያፈርስ (ለምሳሌ፦ የራስ መኮንን ሀውልት) ፣ እንደ አጼ ሚኒሊክ እና እቴጌ ጣይቱ ያሉ ጀግኖች አማራ በመሆናቸው ብቻ በአደዋ ድል በዓል ላይ ሳይቀር ስማቸው እንዳይነሳ ሲያደርግ የአማራ ህዝብ ታሪካዊ ህልውና ከሀገሩ የታሪክ ገጽ ላይ እንዲደበዝዝ ብሎም እንዲጠፋ እያደረገ ነው፡፡ በሀገራችን የተለያዩ ቦታዎች በተለይ በኦሮሚያ ክልል አንዳች ኮሽታ በተፈጠረ ቁጥር አማራው ከለፍቶ ኗሪው እስከ ባለሀብቱ ንብረት ተለይቶ እንደ መስቀል ደመራ ሲነድ የአማራው ኢኮኖሚያዊ ህልውና ስጋት ውስጥ እንደሆነ ማሳያ ነው፡፡ ባለፉት የህዝብ እና ቤት ቆጠራዎች ከሁለት ሚሊየን በላይ የሚሆነው የአማራ ህዝብ ሆን ተብሎ አለመካተቱና በሌሎች ክልሎች የሚኖሩ አብዛኛው የአማራ ተወላጆች አማራ- ጠሉ ስርዓት ባረበበው ስጋት ምክንያት ራሳቸውን እንደአማራ ሳያቆጠሩ የቀሩ መሆናቸው እንዲሁም በአብዛኛው የአማራ ህዝብ ዘንድ የህዝብ ብዛቱ በአማራ-ጠሉ የተገለጸውን እደማይቀበል ትክክለና እና በግልጽ ህዝብ ቆጠራ እንዳልተደረገ እንደሚያምን፤ በዚህም ምክንያት አማራ መያዝ ከነበረበት ተገቢ ፖለቲካዊ ውክልናና ቁመናው ባሻገር በኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ ፖሊሲዎች እና እቅዶች ጭምር ተጎጂ እንዲሆን ተደርጓል፡፡ የአማራ-ጠሉ ጎራ መኳንንት የራሳቸውንም ቋንቋ ከማሳደጉ ርብርባቸው ባልተናነሰ ጉልበት አማርኛ ቋንቋን ለማዳከም እንደሚሰሩ በኩራት ሲናገሩ የአማራ ህዝብ ባህላዊ ህልውና አደጋ ላይ የመውደቁ አንዱ ብቻ ምልክት ነው፡፡

አማራው የህልውና ስጋት የለበትም ማለት ባለፉት ሰላሳ ሶስት አመታት በኢትዮጵያ እነዚህ ድርጊቶች አልተደረጉም ማለት ነው፡፡ አማራው የህልውና ስጋት የለበትም ማለት በሩቁ ዘመን

ከበደኖ እስከ አርባ ጉጉ፣ ከጉራ ፈርዳ እስከ አሶሳ ከቅርቡ ዘመን ደግሞ ከወለጋ እስከ መተከል እንዲሁም በሀጫሉ ሁንዴሳ ሞት ሳቢያ ማንም አማራ በማንነቱ አድራሻ የተላከ የሞት ደብዳቤ አልደረሰውም ማለት ነው። ይህን ሀቅ መካድ ስለማይቻል አማራው የህልውና አደጋ አልደረሰበትም ከማለት ይልቅ የአማራ መሞት ጥፋት መስሎ አይታየኝም ማለቱ የተሻለ ነገር ነው። ፖለቲከኛ ደግሞ ይህን በግልጽ እንደማይል የታወቀ ነውና በአማራው ሞት ቅሬታ እንደሌለበት የሚገልጸው ጋሃድ የሆነውን የህልውና ስጋት በመካድ ነው። የክህደቱ አንዱ ገጽታ “አማራ ብዙ ህዝብ ስለሆነ ሞቶ አያልቅም እና የህልውና ስጋት አለብኝ ማለት አይችልም።” የሚል ማደናገርያ አምጥቶ ልብ ማውለቅ ነው። የዚህ ጽሁፍ አላማም የደሀ ደም ለማይከረፋቸው ፖለቲከኞች የህልውና አደጋን ትርጉም ማስረዳት አይደለም። የጽሁፉ አላማ በህይወት የመኖር መብቱን ጨምሮ ሌሎች የህልውና ስጋቶች የተጋረጡበት የአማራ ህዝብ የህልውና ስጋቱን ለመቀልበስ በሚያደርገው ትግል ተገቢነት ላይ አንዳች ጥርጣሬ ገብቶት እንዳይደናገር ለማሳሰብ ነው።

መስከረም አበራ

ከቃሊቲ ማጎሪያ